KRLB-2-0001

# የአይጦቹ እቅድ



የልጆችን የንባብ ክሂል ለማዳበር ደጋግሞ ማንበብ ጠቃሚ ነው። ይህ ምንባብ የተዘጋጀው ሀረጋትን እና ቃላትን ደጋግሞ የማንበብ ልማድን ለማዳበር ነው። በመሆኑም በየገጹ ታስቦባቸው የገቡና ሶስት ጊዜ የተደጋገሙ ቃላት ወይም ሀረጋት ይገኛሉ።

ታስቦበት የተተወ ባዶ ገጽ

# የአይጦቹ እቅድ

## ለሁለተኛ ክፍል ተማሪዎች የተሰናዳ

የልጆችን የንባብ ክሂል ለማዳበር ደጋግሞ ማንበብ ጠቃሚ ነው። ይህ ምንባብ የተዘጋጀው ሀረጋትን እና ቃላትን ደጋገሞ የማንበብ ልማድን ለማዳበር ነው። በመሆኑም በየገጹ ታስቦባቸው የገቡና ሶስት ጊዜ የተደጋገሙ ቃላት ወይም ሀረጋት ይገኛሉ።

© ኪን የልጆች የትምህርት መርጃ ማዕከል፣ 2014

# መልሶ ትረካ

የዋቢ ስርዓት

ኪን የልጆች የትምህርት መርጃ ማዕከል። (2014) ። የአይጦቹ እቅድ። አዲስ አበባ፣ ኪን።



በአንድ ወቅት አይጦች በድመት በጣም ተቸገሩ፡፡ አንድ ነጭ ድመት አስቸገራቸው፡፡ በጣም አስቸገራቸው፡፡



ድመቱ ድንገት ይመጣና አይጦችን ለቀም አድርጎ ይይዛቸዋል፡፡ ሳያስቡት ድንገት ነው የሚመጣው፡፡ ድንገት ስለሚመጣ ሊያመልጡ አልቻሉም፡፡



ድመቱ አይጦቹን ከያዛቸው በኋላ ይጫወትባቸዋል። ከተጫወተባቸው በኋላ ይነክሳቸዋል። ከነከሳቸው በኋላ ይበላቸዋል።



በድመቱ የተቸገሩ አይጦች ዘዴ ለመፈለግ ተሰበሰቡ። ከድመቱ ለማምለጥ በሚችሉበት ዘዴ ላይ ተነጋገሩ። ድመቱ ሲመጣ የሚያውቁበት ዘዴ ቢኖር ጥሩ መሆኑን ተወያዩ።



ብዙ ተወያይተው አንድ ጠቃሚ ዘዴ አገኙ። ‘ድመቱ አንገት ላይ ደወል ማሰር ጠቃሚ ነው’ ተባባሉ። ድመቱ ሲመጣ ደወሉ ስለሚሰማ ለማምለጥ ጠቃሚ ዘዴ በማግኘታቸው ተደሰቱ።



አይጦቹ እየተደሰቱ አያለ አንድ ትልቅ አይጥ ጥያቄ አቀረቡ። ያቀረቡት ጥያቄ ከባድ ነበር። “ማነው ከእኛ ውስጥ ድመቱ ላይ ደወል የሚያስረው?” ብለው ጥያቄያቸውን አቀረቡ።



የትልቁ አይጥ ጥያቄ ሁሉንም አስደነገጣቸው። ድመቱ ላይ ደወል ለማሰር ሲሄዱ ድመቱ እንደሚይዛቸው ሲያውቁ በጣም ደነገጡ። ከድንጋጤያቸው ሳይወጡ ድመቱ ከተደበቀበት ድንገት መጣ።

የአንደኛ ደረጃ ተማሪዎች ሊያዳብሯቸው ከሚገቧቸው ክሂላት መካከል የማንበብና የመጻፍ ክሂላት ቀዳሚውን ቦታ ይወስዳሉ። እነዚህ ክሂላት በተደጋገመ ልምምድ እና በበቂ የትምህርት መርጃዎች ከተደገፉ በቀላሉ የሚዳብሩ ሲሆን፣ ለአጠቃላይ የትምህርት አቀባበልም ከፍ ያለ ድርሻ ይኖራቸዋል። በቂ አቅርቦት ኖሮ ልምምድ ካልተደረገባቸው ደግሞ ክሂላቱ በቀላሉ የማይዳብሩ ከመሆናቸውም ባሻገር የእድሜ ልክ ችግር ሆነው ይቀጥላሉ። በሚገባ ማንበብ እና መጻፍ በሚችሉና በሚቸግራቸው ልጆች መካከል ሊኖር የሚችል የትምህርት ልዩነት ዘላቂ የመሆን እድሉ ሰፊ ነው። ይህንን ችግር በከፊል ለመቅረፍ ሲባል ኪን የልጆች የትምህርት መርጃ ማዕከል® እነዚህን መሰል የትምህርት መርጃዎች በስፋት አቅርቧል።